

በ: አቪዬል ባሲል
ምሳሌዎች: አቪዬል ባሲል
ዘርፌ: ሀዉጋ
የእድሜ ክልል: አንደኛ ክፍል

שִׂיחָה

ውይይት

ለልደትዎ የትኛውን ፍጹም ስጦታ ማግኘት ይፈልጋሉ? ካላገኙት ምን ይሰማዎታል? የሆነ ነገር በጣም ፈልገው ያውቃሉ ነገር ግን አልተቀበሉትም? ይህ መጽሐፍ የምንጠብቀውን እንድንወያይ ያነሳሳናል – ይህ ለምን ልዩ ስጦታ? የምር ይፈልጉታል ወይስ ሌላ ሰው እንዳለው ስላየን ዝም ብለን እንቀናለን? ስለ ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታዎች እና እነሱን እንድንቋቋም ስለሚረዱን ነገሮች መወያየት ይፈልጉ ይሆናል።

מִשְׂחָק

ፍጹም ስጦታዎች

የራስዎን የቤተሰብ አባላት ምን ያህል ያውቃሉ፣ እና ለእነሱ ፍጹም ስጦታ የሚሆነው ምን ይመስልዎታል – የሚገዙት ነገር ወይስ የልምድ ስጦታ፣ ለምሳሌ፦ አብራችሁ የምታሳልፉት ጊዜ፣ ወይም ምናልባት የሆነ ቦታ የሚደረግ ጉዞ ነው? ጨዋታ ስለመጫወት እና ስለማወቅስ? በእያንዳንዱ ዙር፣ ሁሉም ተሳታፊዎች አንድ ተሳታፊ እንደ ስጦታ ምን ማግኘት እንደሚፈልግ ለመገመት ይሞክራሉ። ግምታቸው በጣም ቅርብ የሆኑት ያሸንፋሉ... ፍጹም የቤተሰብ እቅፍ።

מִשְׂחָק

የሰው የመኪና ጨዋታ

መኪኖች ብቻ በገመድ ተያይዘው ይሽከረከራሉ ያለው ማነው? ሰዎችም ይችላሉ! ከእናንተ ሁለቱ የረጅም ገመድ ሁለቱን ጫፎች እርስ በርሳችሁ በግራ፣ በቀኝ፣ ወደ ኋላ እና ወደ ፊት እየመራችሁ ልትይዙ ትችላላችሁ። ከደከምዎ፣ ትንሽ ያቁሙ እና እንደገና ይጀምሩ።

יְצִירָה

የአብሮነት ጊዜ

ከአባቴ ጋር መኪና ፍጹም ስጦታ ነው›› እና ፍጹሙ ስጦታ ምን እንደሆነ ይገነዘባሉ? ከአባትዎ ወይም ከሌሎች‹‹ የቤተሰብ አባላት ጋር እርስዎ ምን ማድረግ ይፈልጋሉ? የተበላሹ ነገሮችን ማስተካከል፣ የሆነ ነገር መገንባት ወይም መሰብሰብ፣ ወይም ምናልባት አንድ ላይ መሳል፣ መጋገር፣ መትከል ወይም መደነስ ይችላሉ። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ አብራችሁ ጊዜ እሰካሳለፋችሁ ድረስ፣ የሚፈልጉትን ሁሉ ማድረግ ይችላሉ።

הַשְׁרָאָה

Pinterest

[Pinterest – ጥበቦች እና እደ-ጥበቦች እንዲሁም ሌሎች ተግባራት በ PJLibrary Pinterest ላይ ባለው The Perfect Gift ገጽ ላይ ይገኛሉ]